80

# Midroc Newsletter

A BI-MONTHLY PUBLICATION OF THE OFFICE OF THE CHIEF EXECUTIVE OFFICER

This Newsletter provides customers, employees, suppliers, shareholders and the community at large with current information on major performance and other activities of the companies under the leadership of the CEO

Volume 15, Issue No. 80

November 2014 — January 2015

## From the Chairman File



"I invest in Ethiopia because I want to see greater economic development and greater opportunity for all Ethiopians. We need to provide more training and educational opportunities for the youth of Africa as a whole. My companies and I have always supported training and education for all Ethiopians and for all Africans. My companies in Ethiopia are involved in a variety of industries that include construction, manufacturing, mining, hotels and agriculture."

*Sheik Mohammed Hussein Ali Al-Amoudi*

*Source: www.sheikmohammedalamoudi.info*

- ሚድሮክ ወርቅ ማዕድን በ2007 ዓ.ም. በወጪ ንግድ የአንደኛ ደረጃ ልዩ ተሸላሚ ሆነ 2
- ሁዳ ሪል እስቴት ለሞሐ ለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ የገነባው ሕንፃ ተመረቀ 2



*ዶ/ር አረጋ ይርዳው ሽልማቱን በተቀበሉበት ወቅት*



*ሕንፃው በይፋ በተመረቀበት ወቅት*

በውስጥ ገጾቻችን

- ሲ.ኢ.ኦ. የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ተሳተፉ ....................3
- የቴክኖሎጂ ግሩፑ ኩባንያ ሠራተኞች በታላቁ ሩጫ ተሣተፉ......3
- 13ኛው የኩባንያዎች ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ተካሄደ.............4
- ዓመታዊ የስፖርት ውድድር ተጀመረ ....................................4

Inside Pages

- አዲስ ሆም ዴፖ ታላቅ የበዓል ቅናሽ ሽያጭ አካሄደ ................5
- ከሠራተኞች ማኅደር.....................................................6
- ጠቅላላ ዕውቀት.........................................................7
- መልዕክት፣ ከቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር..................................8

# ሚድሮክ ወርቅ ማዕድን በ2007 ዓ.ም. በወጪ ንግድ የአንደኛ ደረጃ ልዩ ተሸላሚ ሆነ



የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች አባል የሆነው ሚድሮክ ወርቅ ማዕድን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደንበኞች በሆኑትና በወጪ ንግድ ላይ በተሰማሩ ድርጅቶች መካከል ባካሄደው ውድድር አንደኛ በመውጣቱ ልዩ ተሸላሚ ሆኗል፡፡

ንግድ ባንኩ በወጪ ንግድ ላይ ተሰማርተው የላቀ የውጭ ምንዛሪ ላስገኙ ደንበኞቹ ታኅሣሥ 30 ቀን 2007 ዓ.ም. በሸራተን ሆቴል ባዘጋጀው የደንበኞች ቀን በ2006 ዓ.ም. ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ የወጪ ሽያጭ በማድረግ ገቢ ያስገኙ ድርጅቶችን በየረድፉ በማመስገንና ሽልማት በመስጠት እንዲበረታቱ አድርጓል፡፡

ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ካስገኙት ሁለት ድርጅቶች መካከል ሚድሮክ ወርቅ ማዕድን በወርቅ አምራችነትና ዌስተርን ዩኒየን በገንዘብ አስተላላፊነት በአንደኛ ደረጃ ልዩ ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰርና የሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃላ.የተ.የግል ማህበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶ/ር አረጋ ይርዳው ሽልማቱን ከንግድ ባንኩ የቦርድ ሊቀመንበርና የጠቅላይ ሚኒስትሩ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ከፍተኛ አማካሪ ከአቶ በረከት ስምኦን እጅ ተቀብለዋል፡፡

ሽልማቱ ተግቶ በመሥራት ላይ ባለው በሚድሮክ ወርቅ ማኔጅመንትና ሠራተኞች ብርታት የተገኘ መሆኑን የገለፁት ዶ/ር አረጋ ይርዳው፤ ይህ ሊሆን የቻለው በሚድሮክ ኢንቨስትመንት ሊቀመንበር በክቡር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ ልዩ አመራርና ድጋፍ መሆኑን በመግለጽ ለሁሉም ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

ሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ኩባንያ ወርቅ በማምረት በ2006 ዓ.ም. ከ152.5 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ገቢ በማስገኘት ለአገሪቱ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ያለ ሲሆን፤ ላለፉት ዓመታት በውጭ ንግድ አምራች ዘርፍ ልዩ ተሸላሚ መሆኑ ይታወሳል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ኩባንያው ለገደንቢ የወርቅ ማምረቻና ሳካሮ የወርቅ ማምረቻ የተባሉ ሁለት ማምረቻዎች ሲኖሩት ከፍተኛ የወርቅ ፍለጋ ሥራ በኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉል ጉምዝና በአማራ ክልሎች በተጠናከረ መልኩ በመሥራት ላይ ይገኛሉ፡፡

# ሁዳ ሪል እስቴት ለሞሐ ለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ የገነባው ሕንፃ ተመረቀ

የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች አባል የሆነው ሁዳ ሪል አስቴት ኃላ.የተ.የግ.ማ. ለሞሐ ለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ ኃላ.የተ.የግ.ማ የገነባው ሕንፃ ኅዳር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. ተመረቀ፡፡

ሁዳ ሪል እስቴት ንፋስ ስልክ በሚገኘው የሞሐ ለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ ለመጋዘንና ለቢሮዎች አገልግሎት የሚውለውን ባለ ሦስት ፎቅ ሕንፃ በ10 ወራት ወሰጥ ገንብቶ በማጠናቀቅ ያስረከበው ድርጅቱ ኅዳር 11 ቀን 2006 ዓ.ም. ያወጣውን የግንባታ ጨረታ በማሸነፍ ነው፡፡



*ሕንፃው በይፋ በተመረቀበት ወቅት*

ሕንፃውን በይፋ የመረቁት የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሠር ዶ/ር አረጋ ይርዳውና የሞሐ ለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ ኃላ.የተ.የግ.ማ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሠር አቶ ጌታቸው ቢርቦ ናቸው፡፡

በምረቃው ወቅት ዶ/ር አረጋ ይህ ግንባታ ከጅምሩ እስከ መጠናቀቁ ድረስ በጥንቃቄና ባልተቋረጠ ክትትል እንዲሁም ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ በመገንባቱ ሙሉ በሙሉ በግንባታ ሥራ ተቋራጭነት ለተሰማራው ለሁዳ ሪል እስቴት ትልቅ ስኬት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ዶ/ር አረጋ አያይዘውም በግንባታው ወቅት ምንም የሥራ መጓተት እንዳይኖር፣ የሰው ኃይል እጥረት እንዳይከሰት፣ የግንባታ ዕቃ አቅርቦት ችግር እንዳይፈጠር፣ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በሙሉ አቅማቸው በመሳተፋቸውና ከአማካሪው ድርጅት ጋር በቅርበት በመስራታቸው ግንባታው በተያዘለት የጊዜ ገደብ መጠናቀቁን ገልፀዋል፡፡

የሞሐ ለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሠር አቶ ጌታቸው ቢርቦ በበኩላቸው የህንፃው ግንባታ ለሁዳ ሪል እስቴት ሲሰጥ ‹‹በጥራትና በተያዘለት የጊዜ ገደብ ተጠናቅቆ እንደምንረከብ እምነት ነበረን›› ካሉ በኋላ ይህ ውጤታማነትም ኩባንያውን በአገሪቱ ታሪክ ቀዳሚ ሊያደርገው እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

የሁዳ ሪል እስቴት ኃላ.የተ.የግ.ማ ዋና ሥራ አስኪያጅ አርክቴክት ቴዎድሮስ ሸዋረጋ ኩባንያው ለግንባታው ባሰማራው የሰው ኃይል፣ የግንባታ መሣሪያና ዕቃዎች ቀንና ሌሊት በመሥራት ሕንፃውን በወቅቱ ሊያስረክብ መቻሉን ገልፀው፤ በግንባታው የተሳተፉትን ባለሙያዎችና የግንባታ ሥራ አማካሪውን ቢጋር አርክቴክት ኢንጂነሪንግ ኸርባን ዲዛይን ድርጅትን ለነበራቸው መልካም የሥራ ግንኙነት አመስግነዋል፡፡

ለሕንፃው ግንባታ ከ16 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገ ሲሆን፤ ሕንፃው ቢሮዎችን፣ መጋዘኖችን፣ ካፌና መፀዳጃ ቤቶችን ያካተተ ነው፡፡

# ሲ.ኢ.ኦ. የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ተልዕኮ ላይ ተሳትፈው ተመለሱ



*የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን አባላቱ ከግብፅ መልስ*

የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር ዶ/ር አረጋ ይርዳው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባዔ አቶ አባዱላ ገመዳ በተመራው የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን በግብፅ ባካሄደው የተሳካ የሥራ ጉብኝት ተልዕኮ ላይ ተሳትፈው ተመለሱ፡፡

ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ጨምሮ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ የፐብሊክ ዲፕሎማሲው ቡድን ከታህሣሥ 6 እስከ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. በግብፅ ባካሄዱት ቆይታ ከግብፁ ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢብራሂም አህላብ እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ሳሜህ ሹክሪን ጨምሮ ታላላቅ ስብዕና ካላቸው በርካታ ግብፃውያን ጋር የተሳካ ውይይት አካሂዷል፡፡

ቡድኑ በግብፅ በነበረው ቆይታ በ15ኛው የግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ምክር ቤት በዓል ላይ ተገኝቶ ከአንጋፋ ዲፕሎማቶችና ምሁራኖች ጋር ባደረገው ውይይት የኢትዮጵያን አቋም በሚገባ አስረድቷል፡፡

በተመሳሳይም ቡድኑ ከእስልምናና ከኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት መሪዎች ጋር በመወያየት የሁለቱን አገራት የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ በጋራ እንደሚሠሩ አረጋግጧል፡፡

የግብፁ ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲ በአል-ኢትሃድ ቤተመንግሥት ቡድኑን ተቀብለው ባነጋገሩበት ወቅት ኢትዮጵያና ግብፅ ግንኙነታቸው በዓባይ ወንዝ ብቻ የታጠረ እንዳልሆነና የትብብር አድማሳቸው ይበልጥ ሊሰፋ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ አያይዘውም ኢትዮጵያና ግብፅ አብረው ውኃ ከሚጠጡበት የዓባይ ወንዝ በተጨማሪ በሃይማኖት፣ በባህል፣ በንግድና በኢንቨስትመንት የተሳሰሩ ሊሆኑ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

ቡድኑ ተልዕኮውን አጠናቅቆ ሲመለስ የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ/ር ቴዎድሮስ አድኃኖም ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ያደረጉ ሲሆን፤ በዚሁ ወቅት አፈ ጉባዔ አባዱላ ገመዳ ቡድኑ በካይሮ ባደረገው ቆይታ የሁለቱን አገራት ግንኙነት የሚያጐለብት ስኬታማ ሥራ ሠርቷል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን ታህሣሥ 14 ቀን 2007 ዓ.ም. በብሔራዊ ቤተ መንግሥት የጉብኝቱን ሪፖርት ባቀረበበት ወቅት የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሣለኝ የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ካደረጉ በኋላ፤ ቡድኑ በአባይ ወንዝ ዙሪያ ከተፋሰሱ አገራት ጋር መነጋገር መቻሉ ዕድለኛ እንደሚያደርገው ገልፀው፤ በቀጣይም የተቋም መልክ ይዞ እንደሚቀጥልና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራውን እንደሚሠራ አረጋግጠዋል፡፡

የቡድኑ አባላትም በግብፅ ቆይታቸው የአገሬው ህዝብ በአባይ ወንዝ ላይ የነበረውን አመለካከት ከመቀየር አኳያ ትልቅ ተልዕኮ መፈፀሙን ገልፀዋል፡፡

## የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያ ሠራተኞች በታላቁ ሩጫ ተሣተፉ

አርባ ሺህ ታዳሚያን የተሣተፉበት መነሻና መድረሻውን ጃንሜዳ ያደረገው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ለ14ኛ ጊዜ እሁድ ኅዳር 14 ቀን 2007 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ተካሄደ፡፡

በዚህ የከተማ ሩጫ ከሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች የተውጣጡ ሠራተኞች ተሣታፊ የነበሩ ሲሆን፤ ውድድሩ ከመጀመሩ በፊት ከዶ/ር አረጋ ይርዳው የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር ጋር በሼራተን አዲስ የማስታወሻ ፎቶግራፍ ተነስተዋል፡፡

ሲኢኦ ኩባንያዎቻቸውን ወክለው በታላቁ ሩጫ ላይ የተሣተፉትን ሠራተኞችንም አመስግነዋል፡፡



# 13ኛው የኩባንያዎች ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ተካሄደ




*ዶ/ር አረጋ ይርዳው አዲሱን ኩባንያ ባስተዋወቁበት ወቅት*

የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች 13ኛው ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ከኅዳር 12 — 15 ቀን 2007 ዓ.ም. መቻሬ ሜዳ በሚገኘው የቴክኖሎጂ ግሩፑ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተካሄደ፡፡

ስብሰባውን በይፋ የከፈቱት የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር ዶ/ር አረጋ ይርዳው የሥራ አፈፃፀም ግምገማው ዓላማ የ2006 ዓ.ም. የሥራ ዕቅድና አፈፃፀም አመዛዝኖ ችግሮችን በማረም በጐ ጐኖችን አጠናክሮ ለመቀጠል የሚያስችል መሠረት ለመጣል ነው ብለዋል፡፡

በስብሰባው የእያንዳንዱ ኩባንያዎች ግብይትና ሽያጭ የአሠራር ሥርዓት፣ የሒሣብ አያያዝና አጠቃቀማቸው፣ የሰው ኃይል ስምሪት፣ በተያዘው የ2007 ዓ.ም. በጀት ዕቅድና የማስፋፊያ ሥራዎች በዝርዝር በየኩባንያዎቹ ዋና ሥራ አስኪያጆች አማካኝነት ቀርበው የተገመገሙ ሲሆን፣ ከተሰብሳቢዎች ለተነሱ በርካታ ጥያቄዎችና ገንቢ አስተያየቶች በቂ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

በስብሰባው ማጠቃለያ ዶ/ር አረጋ ይርዳው በ2006 ዓ.ም. ኩባንያዎቹ ያከናወኑትን አጥጋቢ የሥራ እንቅስቃሴና የተገኘውን ውጤት አድንቀው ኩባንያዎቹ በዓመቱ ባስገኙት የገቢ መጠን ልክ በተዘጋጀው የመተመኛ ስልትና ፖሊሲ መሠረት ተሰልቶ ዓመታዊ የሠራተኞች የደሞዝ ጭማሪ እንደሚደረግ አብራርተዋል፡፡

ዶ/ር አረጋ የኩባንያዎቹ የአመራር አካላትና ሠራተኞች በተያዘው የ2007 ዓ.ም. የበጀት ዓመት ጠንክረው በመሥራት ኩባንያዎቻቸውን ወደ ላቀ ደረጃ እንዲያሸጋግሩና ውጤት እንዲያስመዘግቡ በትጋት መሥራት እንዳለባቸው በአጽንኦት አሳስበዋል፡፡

በመጨረሻም ዶ/ር አረጋ ይርዳው አዲስ የተቋቋመውንና 21ኛ በመሆን ቴክኖሎጂ ግሩፕ ውስጥ የተካተተውን የሚድሮክ ጂ.ኢ.ኦ ኤክስፕሎሬሽን አገልግሎት ኃላ.የተ.የግ.ማ (MIDROC GEO Exploration Service Plc) ኩባንያን በይፋ አስተዋውቀዋል፡፡

በስብሰባው ከሃያዎቹ ኩባንያዎች የተውጣጡ ከ200 በላይ የአመራር አባላት ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

በዓመታዊ ግምገማው ማጠቃለያ ዕለት የስብሰባው ተካፋዮች በጠቅላላ ወደ ቡራዩ ጉዞ በማድረግ በ200 ሺህ ካሬ ሜትር ላይ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋምነት የሚያገለግል የማደሪያ፣ የመመገቢያ፣ የመማሪያ እንዲሁም የመዝናኛ ግንባታ እያከናወነ የሚገኘውን የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲን የሥራ እንቅስቃሴ ጐብኝተዋል፡፡

# በሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች፣ እህትማማችና ተጋባዥ ተቋማት መካከል የሚካሄደው ዓመታዊ የስፖርት ውድድር ተጀመረ



*ዶ/ር አረጋ ይርዳው በዓመታዊው የስፖርት በዓል ላይ ንግግር ሲያደርጉ*

## ዓመታዊ የስፖርት ውድድር ...

በሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕና በተጋባዥ ተቋማት መካከል የሚካሄደው የስፖርት ውድድር ጥር 17 ቀን 2007 ዓ.ም. በመቻሬ ሜዳ ኮርፖሬት ሴንተር ግቢ በቴክ ሣር ቤት እግር ኳስ ቡድንና በአዲስ ኢንተርናሽናል ካተሪንግ እግር ኳስ ቡድን መካከል በተካሄደ የእግር ኳስ ግጥሚያ በታላቅ ድምቀት ተጀምሯል፡፡

የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሠር ዶ/ር አረጋ ይርዳው በበዓሉ መክፈቻ ወቅት በሚድሮክ ኢትዮጵያ ሊቀመንበርና ባለሀብት በሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ የሚመሩት በርካታ ኩባንያዎች የእርስ በእርስ ግንኙነታቸው እንዲጠናከርና እንዲዳብር በስፖርቱ መስክ ትስስር መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን ገልፀው፤ በዚህ ምክንያትም ቴክኖሎጂ ግሩፑ እህትማማች ኩባንያዎችን ያሳተፈ ውድድር ባለፉት ሦስት ዓመታት ማካሄዱን ተናግረዋል፡፡

በውድድሩ ከቴክኖሎጂ ግሩፑ ኩባንያዎች በተጨማሪ ተጋባዥ እህት ኩባንያዎችና የመንግሥት ተቋማት በወዳጅነት መንፈስ ስፖርታዊ ጨዋነትንና ወዳጅነትን በማንፀባረቅ ውድድሩን እንዲያከናውኑ ዶ/ር አረጋ አሳስበዋል፡፡

ለሦስት ወራት በሚቆየው በዚህ የወዳጅነት የስፖርት ውድድር የቴክኖሎጂ ግሩፑን ኩባንያዎች ጨምሮ ከተጋባዥ ተቋማት ዳሽን ባንክ፣ ኒያላ ኢንሹራንስ፣ ናሽናል ሞተርስ፣ አዲስ ኢንተርናሽናል ካተሪንግ፣ ሞሐ ለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ፣ ኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ፣ ኢትዮ ቴሌኮም ደቡብ ምዕራብ ቀጠና፣ ሜጋ ኮንስትራክቲንግ እና ማኔጅመንት፣ ጋልሪየስ፣ ሆራይዘን አዲስ ጐማና ኢትዮ-ሌዘር ኢንዱስትሪ ተካፋይ ይሆናሉ፡፡

ስፖርታዊ ውድድሮቹ በእግር ኳስ፣ በመረብ ኳስ፣ በገመድ ጉተታ፣ በሜዳ ቴኒስ፣ በሩጫ፣ በዱላ ቅብብሎሽ፣ በጠረጴዛ ቴኒስ፣ በቼዝ፣ በዳማና በዳርት የሚካሄዱ ሲሆኑ፤ ወንዶችና ሴቶች ተወዳዳሪዎች ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

በስፖርት በዓሉ መክፈቻ ላይ የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች ከፍተኛ የሥራ አመራር አባላት፣ ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም የተጋባዥ ተቋማት ተወካዮችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል፡፡



ቴክሣርቤት እግር ኳስ ቡድንና አዲስ ኢንተርናሽናል ካተሪንግ እግርኳስ ቡድን

## አዲስ ሆም ዴፖ ታላቅ የበዓል ቅናሽ ሽያጭ አካሄደ



የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች አባል አዲስ ሆም ዴፖ ኃላ.የተ.የግ.ማ የገናና የመውሊድ በዓልን በማስመልከት በሚሸጣቸው ዕቃዎች ላይ ልዩ ቅናሽ በማድረግ ሽያጭ አከናወነ፡፡

ኩባንያው ብሥራተ ገብርዔል በሚገኘው ዋናው ቢሮ ከታህሣሥ 23 እስከ 28 ቀን 2007 ዓ.ም. ለደምበኞቹ በዕቃዎች ላይ ሽያጭ ያከናወነ ሲሆን፤ ጥር 17 ቀን 2007 ዓ.ም. የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሠር ዶ/ር አረጋ ይርዳው በተገኙበት የሠራተኞች በዓል አክብሯል፡፡

በክብረ በዓሉ ዕለት በቅናሽ ሽያጩ ላይ ለተሳተፉ ሠራተኞች የምሥጋና የምሥክር ወረቀት የተሰጠ ሲሆን፤ ዶ/ር አረጋ ይርዳው ለሠራተኞች እያደረጉ ያለውን ክትትልና ድጋፍ በማድነቅ በኩባንያው ዋና ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ ዝናሽ አስራት አማካኝነት ስጦታ ተበርክቶላቸዋል፡፡

# ከሠራተኞች ማኅደር

## የሠራተኞች ቅጥር፣ ዝውውር፣ የለቀቁ፣ በጡረታ የተሰናበቱ፣ ጋብቻ የፈፀሙና ዜና ዕረፍት

### የተቀጠሩ

አቶ ብሩክ ብርሃኑ እና ፀጋዬ ሻውል በላይት ቬኼክል ኦፕሬተር በሚድሮክ ሲኢኦ፤ ሀብታሙ ይልማ ጁኒየር ኤሌክትሪካል ኢንጅነር፣ደስታ ኪለታ ጁኒየር ኢንጅነር /ሲቪል ወርክስ/ በሚድሮክ ሲኢኦ፤ መኮንን ታደሰ ዴይሪ ካትል ማኔጅመንት ኤክስፐርት፣ አዝማች ደገፉ፣ ዮናታን ዑመር፣ አማኑኤል ፀጋዬ ማሽን ኦፕሬተር፣ ሰላማዊት አለባቸው፣ አክሊሉ ግዛውና ኤፍሬም ሙሉ አካውንታንት፣ ኅዳና ታቼ ፐርሰኔል፣ ሲሳይ በቀለ ቬኼክል ኦፕሬተር፣ ሰላማዊት ፈቃደ ፕሮጀክት ኢንጅነር፣ አብዱራህማን አህመዲን፣ ሳሙኤል መኩሪያ፣ ቅድስት አባተና ሜሮን ይገዙ ማርኬቲንግ ኦፊሰር፣ ሰለሞን ግዛው ፋይናንስ ኦፊሰር፣ ሙሉጌታ ፍቃዱና ገብረሚካኤል ነጋሽ ኢንጅነር I፣ አይናለም ፍሪደም ሴክሬተሪ፣ ኑሩ ሞሐመድ ቬኼክል ኦፕሬተር የሥራ መደብ በኤልፎራ ተቀጥረዋል፡፡

አስመሮም ገ/ማርያም በሳይት ኢንጂነር፣ ኢዮብ ገላው ፎርማን፣ ኢዮብ አውራሪስ ሲቪል ኢንጂነር፣ ሰለሞን ገ/እግዚአብሔር፣ አለማየሁ አሻግሬ እና ነጋ ታደሰ ቬኸክል ኦፕሬተር፣ ብሌን መኮንን ማርኬቲን ኦፊሰር፣ ማርታ አስፋው በሲኒየር ሴክሬተሪ፣ ሄለን አየለ ኮንትራክት አድሚኒስትሬሽን ኢንጂነር፣ ፍራኦል በቀለ አቴንዳንት ኦፊስ ፋሲሊቲ ሜንቴናንስ የሥራ መደብ በሁዳ ሪል እስቴት፤ ቢንያም ሙሉ፣ ዳኛቸው አለማየሁ፣ ባሮ ወዳጆ፣ አብዱልቃድር ሙሉ፣ በርሄ ሂሼና ጌታሁን ደርቤ በኮስፒ፤ ዮሀንስ ሀይሌ ማርኬቲንግ ኦፊሰር፣ መሰንበት ፈቃዱ አካውንታንት በቲ.ኤን.ኤ.፤ ሕይወት ስዩም ኦፊስ ሳኒተሪ አቴንዳንት፣ የኂላሸት ማሞ አሲስታንት ከስተምስ ክሊሪንግ ኦፊሰር፣ ሲራክ ተካበና ከበደ ታፈሰ ቬኼክል ኦፕሬተር፣ ድርሻዬ ከበደ ፕሬቴክሽን ኦፊሰር፣ ደስታ ሁቃ እና ከበበ ቅባ ጁኒየር ፕሮቴክሽን ኦፊሰር፣ ኮማንደር ተጐዳን ትዕዛዙ ዳይሬክተር ፕሮቴክሽን ኦፕሬሽን በትረስት፤ ዙላ አብርሀም ማርኬቲንግ ኦፊሰር በብሉ ናይል፤ ፌበን የራስወርቅ በኮስቲንግ ኦፊሰር፣ አባይ በላይ በዌልደር፣ ኤሊያስ ወርቁ በግሪስ ቦይ፣ ስንታየሁ ደሴ በሜካኒክ፣ ማህተም ፍሰሃ እና ግደይ አብርሃም በሾፌር የሥራ መደብ በዩ.ኤ.ኤም ተቀጥረዋል፡፡

ወ/ት ትዕግስት አበራ ጀማሪ ፀሐፊ፣ ወርቁ ኤርሴኖ ኮምፒዩተር ላብ ቴክኒሺያን፣ እያሱ አራጋው ዲሞንስትሬሽን ቴክኒሽያን፣ ምስክር አንተነህ እንግሊዝና አማርኛ መምህር፣ ቤተልሔም ይግዛው፣ በኃይሉ ታደሰ፣ መይሙና ሰይድ፣ ገነት ሰይፉ፣ ፋሲል ጌታሁን፣ ዘላለም ለማ እና ታሪኩ አቶምሳ መምህር፣ አገሪቱ ገ/ጻዲቅ ኬጂ ረዳት መምህር፣ ቅድስት ገበየሁ ኬጂ መምህር፣ ሙሉመቤት ደለለኝ እና ሰላማዊት ዳዊት ሞግዚት፣ ፀዳለ አባተ ረዳት ሱፐርቫይዘር፣ ሔለን ታምሩ ስቶር ኪፐር፣ አህመድ ሙህዬ ፎቶ ኮፒ ማሽን ኦፕሬተር፣ ጌታቸው ታደሰ ኤግዚኪዩቲቭ ትሬሊንግ ኦፊሰር፣ ፀጋው በቀለ ዳታ ኦፊሰር፣ ለማ በየነ ጄኔራል ኤጁኬሽን ኮኦርዲኔተር፣ ቤተልሔም ፍቅረማርያም አካውንታንት፣ ፈዲላ ሙሐጅር ግራፊክስ ዲዛይንና አይዲ ካርድ ኦፊሰር፣ ሽሽጌ በርሔ፣ ዘሃራ ሰይድ፣ የሻረግ መብራቱ፣ ዙፋን ሞላ እና አብዱርሃማን ሞሐመድ አቴንዳንት ክሊኒንግ ሰርቪስ፣ ያሬድ ጣሰው ስቶር ኪፐር፣ በኃይሉ ብርሃኑ ኩክ፣ ሳሙኤል ደበሌ እና ፍቅር ወርቁ ኦፍሴት ማሽን ኦፕሬተር፣ መሐመድ ኢብራሂም ፕሊቲን /ሌተር ፕሬስ/ ኦፕሬተር፣ አለምነሽ ውቤ፣ ትዕግስት ኤርጳሳ፣ ጥሩወርቅ ወልባ አቴንዳንት፣ ሹመት አንዳርጌ የመቁረጫ ማሽን ኦፕሬተር፣ አብረሃም ደጀኔ እና በረከት ብርሃኑ ረዳት ኦፍሴት ማሽን ኦፕሬተር፣ ቤተልሔም ታደሰ ማርኬቲንግ ኦፊሰር፣ ረቂቅ አወቀ አይቲ ላብ ቴክኒሽያን፣ ካሳዬ ጥላሁን መምህር የሥራ መደብ በዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ተቀጥረዋል፡፡

አቶ ሱራፌል ተስፋ ሲኒየር አካውንታንት፣ ረቂቅ ቦጋለ አካውንታንት ደሴ ቅርንጫፍ፣ አስግዶም ገ/ፃዲቅ ሱፐርቫይዘር ቤከር፣ ቅድስት ሸዋፈራሁ እና ስምረት ተፈራ ስቶር ኪፐር፣ ፌቨን ግርማይ ማርኬቲንግ ኦፊሰር፣ ባዩሽ አሸናፊ ሴልስ ፐርሰን፣ ነፃነት ተሾመ ጁኒየር አካውንታንት የሥራ መደብ በኩዊንስ ሱፐርማርኬት፤ በኃይሉ አለማየሁ ቬኸክል ኦፕሬተር፣ ፀጋዬ ብርሃኑ ኦፊስ ፋሲሊቲ ሜንቴናንስ አትክልተኛ የሥራ መደብ በሰሚት ፓርትነርስ ተቀጥረዋል፡፡

### የለቀቁ

አቶ የትምሰው ስዩም፣ ሲሳይ ፉፋ፣ ሰርካለም አስፋው ከሚድሮክ ወርቅ፤ ደሳለኝ አሰን፣ ፀሐይ ደመቀ፣ መላኩ ማቲዎስ፣ ስንዱ ፈጠነ፣ ተፈሪ መኮንን እና ክፍሌ ወ/ዮሐንስ ከኤልፎራ፤ ፍቅሩ አስናቀ፣ ከበረ ተ/ማርያም ከሚድሮክ ወርቅ፤ ዳናይት ካላዩ፣ ሙሉጌታ ዴሮና ሰርካለም አሰፋ ከሁዳ ሪል እስቴት፤ ሄለን ንጉሱ እና ድሉ ሞገስ ከትረስት፤ ኢትዮጵያ ሙሉጌታ፣ እድሉ ገብሬ እና አልማዝ አብዲ ከብሉ ናይል፤ ሙሉእመቤት ኤርሚያስ፣ ይልማ ፈቃዱ፣ ቴዎድሮስ መሰለ እና ንዋይ አስራት ከዩ.ኤ.ኤም በራሳቸው ፈቃድ ለቀዋል፡፡

ወ/ሮ አበባ መኩሪያ፣ የሺ ተክሌ፣ ወይንሸት ገመቹ፣ አፀደ ተክሌ፣ ረድኤት ወርቁ፣ አዲስ ሰይፉ፣ ሱራፌል ብርሃኑ፣ ተመቸው መኮንን፣ አምሮት ደበበ፣ ፈቃዱ ካሳዬ፣ መስፍን መላኩ፣ ምህረት ማሞ፣ እንዳልካቸው አቡ፣ ተስፋሁን እሸቱ፣ ፍሬሕይወት አሰፋ፣ህይወት ቢረዳ፣ አምሳል ተስፋዬ፣ ሳሙኤል ማሞ፣ ምትኩ ውቤ፣ ቀለሟ መኮንን፣ ሮቤል ተፈረደኝ፣ አበበች ውበቱ እና ማሜ ተፈራ ከዩኒቲ ከዩኒቨርሲቲ፤ ሳባ ይመር ከኩዊንስ ሱፐርማርኬት በራሳቸው ፈቃድ ለቀዋል፡፡

### የተዛወሩ

ወ/ት ሰላማዊት አበራ ማናጀር ሂዩማን ሪሶርስ ከሲኢኦ ወደ አዲስ ሆም ዴፖ፣ ትዕግሥት ገብሩ ማናጀር ሂዩማን ሪሶርስ ሰርቪስ ከሲኢኦ ወደ ሁዳ፣ ሰለሞን ከበደ ማናጀር ከስተመር ሰርቪስ ከሲኢኦ ወደ ዩ.ኤ.ኤም፣ አምሐ ይልማ ማናጀር ሂዩማን ሪሶርስ ሰርቪስ ከሲኢኦ ወደ ሬይንቦ፣ ሰለሞን ደጀኔ ዋና ስራ አስኪያጅ ከሲኢኦ ወደ ትረስት፣ እስካጥናፍ መዝገቤ ማናጀር ኮርፖሬት ፐብሊክ ሬሌሽን ሰርቪስ ከኤም.ቢ.አይ ወደ ሲኢኦ፣ ታደለች ለማ ማናጀር ማቴሪያልስ ማኔጅመንት ሰርቪስ ከዩኒቲ ወደ ሲኢኦ፣ አለምፀሐይ ኃይሌ ማናጀር ኮርፖሬት ማርኬቲንግ ኤንድ ሴልስ ሰርቪስ ከአዲስ ሆም ዴፖ ወደ ሲኢኦ፣ ጥሩ ታሹ ማናጀር ኮርፖሬት ኳሊቲ አሹራንስ ሰርቪስ ከዴይላይት ወደ ሲኢኦ፣ ወንድማገኝ መርጊያ ሱፐርቫይዘር ቴክኒካል ሰርቪስ ከሲኢኦ ወደ ዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ፤ ከበደ ዋጋሪ ዳይሬክተር ሂዩማን ሪሶርስ ከኤልፎራ ወደ ሰሚት ኢንጂነርድ፣ ሀብታሙ ኢፋ ማናጀር ሂዩማን ሪሶርስ ከኤልፎራ ወደ ዴይላይት፣ ፍፁም ኃይሉ ዳይሬክተር ማቴሪያል ማኔጅመንት ከኤልፎራ ወደ አዲስ ሆም ዴፖ፣ ሳሙኤል አረጋይ ማናጀር ከኤልፎራ ወደ ዴይላይት፣ ታሪኩ ነገራ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከሚድሮክ ወርቅ ወደ ኤልፎራ፣ ትግስት ገብረፅዮን ዳይሬክተር ማቴሪያል ማኔጅመንት ከዴይላይት ወደ ኤልፎራ፤ ኤልሣቤጥ ደማ ማናጀር ሂዩማን ሪሶስር ሰርቪስ ከሁዳ ሪል እስቴት ወደ ትረስት፣ ካሱ ሀይሌ ማናጀር ፋይናንሻል ሰርቪስ ከሁዳ ወደ ሴፕኮ፣ ብዙነህ ተሰማ ተ/ጀነራል ማናጀር ቢዝነስ ዴቨሎፕመንት ኤንድ ፕሮጀክት ማኔጅመንት ከኤልፎራ ወደ ሁዳ፣ ኃይሌ አብርሀ ማናጀር ፋይናንስ ሰርቪስ ከሴፕኮ ወደ ሁዳ፤ መኮንን ገ/መድህን ከብሉናይል ወደ ኮስፒ፣ሳራ ገ/መድህን ከዴይላይት ወደ ኮስፒ ተዛውረዋል፡፡

ወይንሸት አብዲ ማናጀር ፋይናንስ ከቲ.ኤን.ኤ. ወደ ኤም.ቢ.አይ፣ ፍቅርተ ያለው ማናጀር ሂዩማን ሪሶርስ ከአዲስ ሆም ዴፖ ወደ ቲ.ኤን.ኤ.፣ አለሙ መካሻ ማናጀር ፋይናንስ ከሬይንቦ ወደ ቲ.ኤን.ኤ.፤ ዮሐንስ እጅጉ ዳይሬክተር ከስተምስ ክሊሪንግ ኦፕሬሽን ከትረስት ወደ ኮስፒ፣ ቅድስት መኰንን የሰው ኃይል አገልግሎት ሥራ አስኪያጅ ከትረስት ወደ ሲኢኦ፣ ወንዲፍራው አድማሱ ዳይሬክተር ከስተምስ ክሊሪንግ ኦፕሬሽን ከሚድሮክ ጐልድ ወደ ትረስት፣ አመሐ ደሳለኝ እና ደስታ በዛብህ አሲስታንስ ከስተምስ ክሊሪንግ ኦፊሰር ከሚድሮክ ጐልድ ወደ ትረስት፤ ነፃነት በላይ ማናጀር ሂዩማን ሪሶርስ ከዩ.ኤ.ኤም ወደ ሰሚት፣ ተስፋዬ ባይሳ ከዩ.ኤ.ኤም ወደ ሬይንቦ፣ ዝናቡ ወ/ዮሐንስ ከዩ.ኤ.ኤም ወደ ኤም.ቢ.አይ፣ ዘለአለም አመነሸዋ ከዩ.ኤ.ኤም ወደ ኤልፎራ፣ ተስፋዬ የሺጥላ፣ ግዛቸው ማሞ፣ አለባቸው ታረቀኝ ከሬይንቦ ወደ ዩ.ኤ.ኤም፣ ስንታየሁ ይርሳው ከሴፕኮ ወደ ዩ.ኤ.ኤም፣ ገበየሁ ምህረቴ ከኩዊንስ ወደ ዩ.ኤ.ኤም፣ ተስፋዬ ፈለቀ ከሰሚት ወደ ዩ.ኤ.ኤም፣ ሰለሞን ከበደ ከሲኢኦ ወደ ዩ.ኤ.ኤም፤ ታደለች ለማ ሲኒየር ሱፐርቫይዘር ከዩኒቲ ወደ ሲኢኦ፣ ማርታ ከበደ ጀማሪ ላቦራቶሪ ቴክኒሽያን፣ ወንድሙ መርጊያ ካምፓስ/ፋሲሊቲና ኢኪዩፕመንት ሜንቴናንስ ማኔጀር፣ አስቴር ከበደ ኬጂ ረዳት መምህር ተዛውረዋል፡፡

ኤፍሬም ታደለ ዳይሬክተር ሂዩማን ሪሶርስ ሰርቪስ ከኩዊንስ ወደ ኤልፎራ፣ ገበየሁ ምህረቴ ማናጀር ማቴሪያልስ ማኔጅመንት ኤንድ ስቶር ሰርቪስ ከኩዊንስ ወደ ዩ.ኤ.ኤም.፣ ሙሉዓለም ደምሴ ማናጀር ሂዩማን ሪሶርስ ሰርቪስ ከኩዊንስ ወደ ዋንዛ፣ ደረጀ ደጀኔ ማናጀር ማቴሪያልስ ማኔጅመንት ኤንድ ስቶር ሰርቪስ ከኩዊንስ ወደ ኮስፒ፣ ያለምዘውድ አስማማው መርቸንዳይዝ ኦፊሰር ከኩዊንስ ወደ ሬይንቦ፤ ወይንሸት ቶጋ በፋይናንስ ማናጀር ከኤልፎራ ወደ ሰሚት፣ ተዛውረዋል፡፡

### የተሰናበቱ

አቶ ዮሴፍ ደረጀ ከዩ.ኤ.ኤም፤ ኤርሚያስ ወርቅሉል፣ ክንፈ ዮሐንስ፣ ኃይማኖት ዋለ፣ ዮናስ አባታ፣ ጀማል ሁሴን፣ ህሊና ጌታቸው፣ ገናነው ከበደ፣ አንዱአለም ግርማ፣ መስፍን አሻግሬ እና መንግስቱ ውቡ ከዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ በድርጅቱ ተሰናብተዋል፡፡

### ጋብቻ የፈፀሙ

ወ/ት ኤዶም ሐይሌ ከአቶ ይትባረክ የማነ ከትረስት፣ አቶ ሳልማን አሰፋ እና ወ/ት ወርቃየሁ በየነ ጋብቻ ፈጽመዋል፡፡ ለሥራ ባልደረቦቻችን ጋብቻቸው የአብርሃምና የሣራ እንዲሆንላቸው እየተመኘን የደስታቸው ተካፋይ መሆናችንን እንገልጻለን፡፡

### ጡረታ የወጡ

ወ/ሮ ሰናይት አስፋው እና አቶ ተካ ኃይሌ ከሚድሮክ ወርቅ፤ አቶ ሙሴ በሪሶ እና አቶ ሸዋንግዛው ዘውገ ከኤልፎራ በጡረታ ተገልለዋል፡፡ ለሥራ ባልደረባችን ቀሪው ዕድሜዎ መልካም የዕረፍት ጊዜ እንዲሆንልዎ እንመኛለን፡፡

### በሞት የተለዩ

አቶ ህርፓዬ ዋሬ ከሚድሮክ ወርቅ፤ አቶ ገብሩ ወንድሙ ከኮስፒ፤ አቶ ጀልዱ ሄብሮ ከትረስት፤ አቶ አዲስ ገ/መስቀል፣ ወ/ሮ ትዕግስት እሸቱ፣ ወ/ት በላይነሽ ወ/ስላሴ ከዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ በሞት ተለይተዋል፡፡ ለሥራ ባልደረቦቻችን ቤተሰቦች እግዚአብሔር መጽናናትን እንዲሰጣቸው እየተመኘን የሐዘናቸው ተካፋይ መሆናችንን እንገልጻለን፡፡

# ጠቅላላ ዕውቀት

## የደም ዓይነቶች

ምንም እንኳን የማንኛውም ሰው ደም የተሰራበት መሰረታዊ ነገር አንድ ዓይነት ቢሆንም ያንዱ ሰው ደም ከሌላው ይለያል፡፡ የደም ዓይነት የተለያየ እንዲሆን የሚያደርገው ነገር በቀይ የደም ሴሎች የውጭው አካል ላይ ያሉ አንቲጂን የሚባሉ ነገሮች ናቸው አንቲጂን ማለት ማንኛውም ነገር ሆኖ ነገር ግን የሰውነትን በተፈጠሮ በሽታ የመከላከል አቅም ወይንም ኢሚዩን ሲስተም ማስቆጣት የሚችል ነገር መሆን አለበት ለምሳሌ ቫይረስ ባክቴሪያ ኬሚካል የአበባ ብናኝ አልያም ሌሎች ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ደም በሰውነታችን ውስጥ የሚዘዋወር ፈሳሽ ሲሆን ዋና ጥቅሙም ምግብና ኦክሲጂን ለተለያዩ የሰውነታችን ህዋሳት ማቀበልና ከህዋሳት ውስጥ የሚወጣውን ካርቦን ዳይ ኦክሳይድና ሌሎችንም ቆሻሻዎች ማስወገድ ነው የሰውነት በተፈጥሮ በሽታ የመከላከል አቅምም ያለው በደም ውስጥ ነው ደም ፈሳሽ ቢመስልም በውስጡ ግን የተለያዩ ሴሎችንና ሌሎች ፕሮቲኖችን ይይዛል እነዚህም ሴሎች ደም ከውሃ ትንሽ ከፍ ያለ ዴንሲቲ እንዲኖረው ያደርጋል አንድ 70 ኪሎ ግራም የሚመዝን ሰው በአማካይ 5 ሊትር ወይም አንድ ጋሎን ደም ይኖረዋል፡፡

ደም የተሰራው ከምንድን ነው ?

፩. ሴሎች/ህዋሳት- እነኚህ ከጠቅላላው ደም 45% ሲሆኑ አብላጫውን የሚይዙት ቀይ የደም ሴሎች ናቸው የደም ሴሎች የሚሰሩት በአጥንት መቅኔ ውስጥ ነው፡፡

1. ቀይ የደም ሴሎች /Red Blood Cells-RBCs/
2. ነጭ የደም ሴሎች /White blood cells or leukocytes/
3. ፕላትሌትስ /Platelets/

፪. ፕላዝማ — ይህ ፈሳሹ የደም ክፍል ሲሆን በአብዛኛው የተሰራው ከውሃ ሆኖ ፕሮቲኖችን እና ሌሎች ነገሮችን ይይዛል ፕላዝማ ከጠቅላላው ደም 55% ይሆናል፡፡

ቀይ የደም ሴሎች ኦክሲጂን ለመሸከም የሚያስችላቸው ሂሞግሎቢን የተባለው ሞለኪውል አላቸው በደም ውስጥ ያለው የቀይ የደም ሴሎች መጠን ሄማቶክሪት ይባላል ይሄን ቃል ብዙ ጊዜ በላቦራቶሪ ምርመራ ላይ እናየዋለን መደበኛ መጠኑም 45% ነው የደም ማነስ በሽታ በሚኖርበት ጊዜ መጠኑ ከዚህ ያንሳል፡፡

ነጭ የደም ሴሎች በዋናነት የሰውነትን በተፈጥሮ በሽታ የመከላከል አቅም የሚገነቡት ናቸው ብዙ አይነት ነጭ የደም ሴሎች አሉ ሥራቸውም እንዲሁ ይለያያል ፕላትሌትስ ደም በሚፈሰን ጊዜ ደም እንዲረጋ የሚያደርጉት ናቸው፡፡

በቀይ የደም ሴሎች ላይ ያሉትን የተለያዩ አንቲጅኖች የተለያየ ዓይነት ደም እንዲኖረን ያደርጋሉ በዚህም ምክንያት 8 የደም ዓይነቶች አሉ በአብዛኛው የሚታወቁት አራቱ የደም ዓይነቶች ናቸው እነሱም ኤ.(A) ቢ.(B) ኤቢ.(AB) እና ኦ.(O) ናቸው ነገር ግን ሌላ Rh የሚባል አንቲጂን አለ አንዳንድ ሰዎች ይሄ አንቲጂን ሲኖራቸው ሌሎች ደግሞ የላቸውም ስለዚህ በመደበኛው የደም አይነት ላይ Rh ያላቸው (Rh +) እና የሌላቸው(Rh -) እያልን ስንከፋፍለው 8 የደም ዓይነት ይኖራሉ ማለት ነው፡፡

A +, A -, B +, B — , AB + , AB -, O +, O —

ከዚህ በታች ያለው ምስል የበለጠ ግልፅ ያደርገዋል

“A” የደም ዓይነት A የተባለ አንቲጂን ሲኖረው ፀረ-B የሆነ አንቲቦዲ በፕላዝማ ውስጥ ይኖረዋል ያማለት ቢ. የደም ዓይነት ወደ ሰውነታችን ቢገባ ፀረ-ቢ. አንቲቦዲዎች ጥቃት ያደርሱበታል ማለት ነው ለዚህም ነው በደም ልገሳ ጊዜ የሚለገሰው ደም ከበሽተኛው ደም ጋር አንድ ዓይነት መሆን ያለበት፡፡

“B” የደም ዓይነት B የተባለ አንቲጂን ሲኖረው ፀረ-A የሆነ አንቲቦዲ በፕላዝማ ውስጥ ይኖረዋል፡፡

“AB” የደም ዓይነት A እና B አንቲጂን ሲኖረው ምንም ዓይነት አንቲቦዲ አያመርትም ምክንያቱም እራስን ማጥቃት ይሆናል፡፡

“O” የደም ዓይነት ምንም ዓይነት አንቲጂን የሌለው ሲሆን ፀረ-A እና ፀረ-B አንቲቦዲዎች ይኖሩታል፡፡

“AB” የደም ዓይነት ምንም ዓይነት አንቲቦዲ ስለማያመርት ከሁሉም የደም አይነት መቀበል ይችላል የዚህ አይነት ደም ያለው ሰው ሁለገብ ተቀባይ ይባላል/Universal Recipient/፡፡

“O” የደም ዓይነት ምንም ዓይነት አንቲጂን ስለማይኖረው ለሁሉም ሰው ሊሰጥ ይችላል ስለዚህም ኦ. የደም አይነት ያለው ሰው ሁለገብ ለጋሽ /Universal Donor/ ይባላል፡፡

## የደም ዓይነት እና የአመጋገብ ሥርዓት

የተመገብነው ምግብ በአንጀታች ውስጥ ከተፈጨ በኂላ በደማችን አማካኝነት ወደተለያዩ የሰውነታችን ክፍሎች ይሠራጫል፡፡

በዚህም ሂደት ውስጥ ምግባችን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ንጥረ ነገሮች ከደማችን ጋር ኬሚካላዊ ግንኙነትና ውሕድ ይፈጥራሉ፡፡

ይህንንም ተከትሎ ከደማችን ዓይነት ጋር የሚስማማ ምግብ ከተመገብን የምግብ የመላም ሂደት ሊፋጠን፣ አላስፈላጊ ክብደት ልንቀንስ፣ የላቀ ጉልበት ሊኖረን እንዲሁም የበሽታ የመከላከል ዓቅማችንም ሊዳብር ይችላል፡ ፡ከዚህ በመቀጠልም ከእያንዳንዱ የደም ዓይነቶች ጋር የሚጣጣሙ የምግብ ዓይነቶችን እንጠቅሳለን፡፡

1) የ ኦ (O)ደም ዓይነት የአመጋገብ ስርዓት ይህ የደም ዓይነት ከሌሎች ቀድሞ የነበረ ጥንታዊ ሲሆን ከእንስሳት አዳኞች የተወረሰ የደም ዓይነት ነው፡፡

   የዚህ ደም ባለቤቶች ዓሣ፣ የባህር ምግብ፣ ቀይ ስጋ፣ ጨው፣ ዶሮ፣ ሲኳር ድንችና የመሳሰሉትን ምግቦች እንዲያዘወትሩ ይመከራል፡፡ በዚያውም ልክ ዕንቁላል፣ የእንስሳት ተዋጽኦዎች፣ ስንዴና ባቄላን ከገበታቸው ማራቅ አለባቸው፡፡

2) የ ኤ (A) ደም ዓይነት የአመጋገብ ስርዓት ይህ የሰው ልጆች ወደ እርሻ ሲገቡ በተፈጠረው የአመጋገብ ለውጥ ምክንያት የተከሰተ የደም ዓይነት ነው፡፡ በዚያ ዘመንም የሰው ልጆች ለመኖነት ፊታቸውን ወደ አትክልቶች በማዞራቸው ምክንያት በጊዜ ሂደት እጅግ የዳበረ የምግብ ማላም ስርዓትን አዳበሩ፡፡ በአንጀታችው ውስጥ የሚገኙት የባክቴሪያዎች ዓይነትና ቁጥርም እጅግ ተበራከተ፡፡ የዚህ ደም ባለቤቶች ፖም፣ አቮካዶ፣ ሰላጣ፣ ካሮት፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ባቄላ፣ እርጎ፣ የስንዴ ዳቦና ፓስታ እንዲመገቡ ይመከራል፡፡ ነገር ግን እንቁላል፣ ሥጋ እና ሌሎች የእንስሳት ተዋጽኦዎችን በተገቢው መንገድ ለማብላላት አንጀታቸው አልዳበረም፡፡

3) የ ቢ (B) ደም ዓይነት የአመጋገብ ሥርዓት የጥንቶቹ አዳኞች ወደ ሒማሊያስ ተራሮች በመሰደድ እንስሳትንም በማላመድ የአርብቶ አደር ሕይወትን መምራት ሲጀምሩ የተፈጠረ የደም ዓይነት ነው፡፡

   ቀይ ስጋ፣ ዓሣ፣ እርጎ፣ ዓይብ፣ ወተት፣ ሙዝ፣ አረንጓዴ ቅጠላማ አትክልቶች፣ ወይንና አናናስ ተስማሚ ከሚባሉት ምግቦች መካከል ሲጠቀሱ ዶሮ፣ ስንዴ፣ ቲማቲም እንዲሁም ለውዝ እንዳይመገቡ ይመከራል፡፡

4) የ ኤቢ (AB) ደም ዓይነት የአመጋገብ ሥርዓት ኤቢ የደም ዓይነት በቅርብ ጊዜ የተከሰተ ሲሆን ከዓለም ህዝብም በአምስት ፐርሰንቱ ውስጥ ብቻ ይገኛል፡፡

የዚህ ደም ባለቤቶች ሥጋንና ሌሎች የእንስሳት ተዋጽኦዎችን መፍጨት ቢችሉም የጨጓራቸው አሲድ መጠን ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት የተመገቡት ምግብ በስብ መልክ ይከማቻል፡፡

ፍራፍሬዎችና አረንጓዴ አትክልቶች፣ ሀብሀብ እና ወይን፣ እንደ ቱና እና ሰርዲን ያሉ የባህር ምግቦችን ማዘውተር ተገቢ ሲሆን ከበቆሎ፣ የበሬና አሳማ ሥጋ እንዲሁም ከአልኮሆልና ቡና መራቅ ያስፈልጋቸዋል፡;

*Source: www.Medical Advice*

# መልዕክት፣ ከቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር

## የዲፕሎማሲው ተልዕኮ ለተሻለ መተማመን!

በታላቁ የአባይ ወንዝ ላይ የዛሬ ሦስት ዓመት የተጀመረው ታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ሐውልት ነው። ድኅነት ለዘመናት በተንሰራፋበት አገር ውስጥ ይህንን ታላቅ ግድብ ለኃይል ማመንጫነት በማዋል አገሪቱ ወደ ተሻለ ደረጃ አድጋ ሕዝቦቿ የሚጠቀሙበትን መንገድ መፍጠር የሁሉም ቀና አሳቢ ዜጎች አመለካከት ሊሆን ይገባል።

ለግድቡ እውን መሆን የመንግሥትና የመላ አገሪቱ ሕዝቦች በጋራ መንቀሳቀስ እጅግ የሚያስደስት ቢሆንም በአባይ ውሃ ተጠቃሚ የሚሆኑት አገራት ላይ ግን ስጋት እንዳሳደረ ሲደመጥ ቆይቷል። ይሁንና ኢትዮጵያ ማንኛውንም አገር የመጉዳት አቅጣጫ ሳትከተል በውሃ ክፍፍል ፍትሀዊነት ላይ የተመረኮዘ ዓላማ ስታራምድ እንደነበር ይታወቃል።

ይህንኑ የፍትሀዊነት ዓላማ ለማስገንዘብ መንግሥት በተደጋጋሚ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ሲጠቀም የቆየ ቢሆንም በተጠናከረ መልኩ ለመቀጠል ያመች ዘንድ አንድ ግዙፍ የዲፕሎማሲ ቡድን በማዋቀር ከፍተኛ የግንኙነትና የውይይት ተግባር እንዲከናወን እድል ተፈጥሯል።

የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ቡድን ታላላቅና ስመጥር የሆኑ ታዋቂ ሰዎች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ ምሁራን፣ የሲቪል ማኅበራት ተጠሪዎች የመገናኛ ብዙሀን አባላትና የኪነጥበብ ባለሙያዎች የተካተቱበት ሲሆን፤ እነዚህ የቡድኑ አባላት ከመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር አስቀድመው በመወያየት ወደ ግብፅ በመጓዝ ኢትዮጵያ እያራመደች ያለውን የጋራ ተጠቃሚነት አቅጣጫ በእጅጉ አስገንዝበዋል።

በመሆኑም ከግብፅ ፕሬዚዳንት፣ ከፖለቲከኞች፣ ከምሁራን፣ ከሃይማኖት አባቶችና ከህብረተሰቡ ጋር ውይይት በማድረግ ውጤታማ ተግባር ተከናውኗል፤ ተልዕኮውም የተሻለ መተማመንን አስገኝቷል።

የቡድኑ አባላት በውይይቱ ያደረጉት ተሳትፎ ዜጎች ለአገራቸው ማበርከት ከሚገባቸው ድርሻ አንዱ ነው። ስለዚህም አገሪቱ ለተያያዘችው የመልማትና ከጐረቤት አገሮች ጋር በሰላምና በወዳጅነት ለመኖር ለምታደርገው ጥረት ዜጐች የበኩላችንን እገዛ ልናደርግ ያስፈልጋል።

የቡድኑ አባል በመሆን መሳተፌ መላው የቴክኖሎጂ ግሩፕ ሠራተኞች ለዚህ አቢይ ፕሮጀክት መሣካት ያለንን ቁርጠኝነት አመላካች እንደሆነ አምናለሁ።



ዶ/ር አረጋ ይርዳው
Dr. Arega Yirdaw
ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር፣ ሚድሮክ ኢትዮጵያ
Chief Executive Officer, MIDROC Ethiopia

*Address:*
*MIDROC Ethiopia Technology Group*
*Office of the Chief Executive Officer,*
*Fax: +251-11-371-5988 / 372-4977*
*P.O. Box: 5787, Addis Ababa Ethiopia*
*E-mail: ceomidroc@ethionet.et*
*Website: www.midroc-ethiotechgroup.com*

*በነፃ የሚታደል* *(Distributed at no Cost)*